የሰ/መ/ቁ. 45170

ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- የቅድስተ ማሪያም አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት አመልካች ያለአግባብ የሥራ ውል አቋርጦብኛል ተገቢው ካሣና ጥቅማጥቅም ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የክረምት ሥራ እንድትሰራ መመሪያ ተሰጥቷት እያለ ያለፈቃድ ወይም በቂ ምክንያት ከሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ሥራ ላይ ባለመገኘቷ የሥራ ውል የተቋረጠው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1//ለ/ መሰረት ነው ሲል ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ጊዜው የመምህራን የዓመት እረፍት ጊዜ ነው በማለት ከሥራ መቅረቷን የተቀበለች ቢሆንም መምህራን በክረምት ወራት ሙሉ ለሙሉ እረፍት ስለመሆናቸው በአዋጅ፣በደንብ ወይም በመመሪያ የተደነገገ የለም፣አሰሪ ስራ እንዲሰራ መመሪያ ከሰጠ መሥራት ይጠበቅበታል በሚሉ ምክንያቶች የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ መምህራን በክረምት ወራት እረፍት እንደሚያደርጉ ሲሰራበት የቆየ ልምድ ነው በዚህ መዝገብም የቀረቡት ማስረጃዎች ይህንኑ ያረጋግጣሉ ተጠሪም በእረፍት ወቅት ሥራ ላይ አለመገኘታቸው የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሊሆን አይገባም የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር የሥራ ውል ያለአግባብ ተቋርጧል በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ለተጠሪ የካሣ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት ጊዜ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የሰራተኛ የዓመት እረፍት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በተደነገገው አግባብ በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚወሰን እንጅ ሰራተኛው በዘፈቀደ የሚወስነው አይደለም፣በት/ቤቱ ደንብ መሰረት የዓመት እረፍቷን በነሐሴ ወር ወስዳለች እንዲሁም የ2000 ዓ.ም የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ተከፍሏል በሚሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክቷል፡፡

ሰበር ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ ከአዋጅ አንቀጽ 13/1/ አንፃር ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ክርክር በማጠናከር የክረምት ወራት ለመምህራን በተለየ ሁኔታ የእረፍት ጊዜ እንደመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለመሥራት ግዴታ የለብኝም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቃለች፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ ለማየት የተቻለው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ በክረምት ወቅት እንድታስተምር

መመሪያ ተሰጥቷት ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች በሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የክረምት ትምህርት ለመስጠት አመልካች ከተወሰኑ መምህራን ጋር ውይይት በማድረግ በስምምነት የማስተማር ሥራ ሲያከናውኑ እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ይህውም ሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ የተወሰነ ስለመሆኑ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ መልክ ተጠሪ ፈቅዳ ግዴታ የገባች ስለመሆኑ በዚሁ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አላገኘንም፡፡ ከዚህም ሌላ ተጠሪን የሚያስገድድ ግልጽ መመሪያ ወይም ደንብ ስለመኖሩ አመልካች አላስረዳም፡፡

ስለሆነም ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ በክረምት ወቅት ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ አልሆነችም ተብሎ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/1/ የተመለከተውን ግዴታ ጥሳለች ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ በፍሬ ነገርም ሆነ በሕግ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በዚሁ ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04326 በ01/07/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት